# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 25

ለአንድ ወር ያህል በእረፍት ምክንያት ሳይቀርብ የሰነበተው የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ ስርጭት በዛሬው ዕለት የተለመደውን ስርጭቱን ያቀርባል።በቅድሚያ ግን ለሁሉም አድማጮቻችን እንኳን ለዛሬው ቀን አደረሳችሁ እንላለን።

በራዲዮ ስርጭቱ ከሚቀርቡት አበይት ዝግጅቶቻችን መካከል የስነጽሑፍ ክፍላችን የሚያቀርበው አገር እንዴት ሰነበተች የሚለው አምዳችን ሲሆን በዛሬውም ስርጭታችን በዚሁ ርዕስ የተጠናቀረውን ይዘን ብቅ ብለናል።ስርጭታችንን እስከመጨረሻው ትከታተሉት ዘንድ በአክብሮት እንጠይቃለን አስተያዬታችሁንም እንድትለግሱን የዘወትር ጥያቄያችንን አሁንም እንደግማለን።

ከመግቢያችን ላይ ለእረፍት መውጣታችንን ስንገልጥ የትውልድ አገራችን፣የኢትዮጵያ ሁኔታ እረፍት የሚሰጥ ሆኖ ሳይሆን በአለፈው ዓመት በትምህርት ላይ የከረሙ ልጆችና በሥራ የተዳከሙ ቤተሰቦች በዓመት አንድ ጊዜም ቢሆን ባለንበት አገር ለተወሰነ ሳምንት እርፍት ማድረጉ አስፈላጊ በመሆኑ ፕሮግራማችንን ለማቋረጥ በመገደዳችን እንጂ እንደ ደላው አገር ተወላጅ፣በተለይም ኢትዮጵያ ባለችበት የሞት የሽረት ወቅት መዝናናት አምሮን እንዳልሆነ ለመግለጽ እንወዳለን።

በእረፍቱ የሳምንታት ዕድሜ ለማቅረብ ያልቻልነውን ያገራችንን ሁኔታ አድማጮች ከሌላው የዜና ስርጭት የተከታተሉት መሆኑን በማመን በመደጋገም ጊዜያቸውን ከማባከንና ከማሰልቸት ይልቅ የሰሞኖቹን ዋና ዋናዎቹን ጠቅለል አድርጎ ማቅረቡን መርጠናል።

የአገራችን ሁኔታ ከድጡ ወደማጡ እዬሆነ ሄደ እንጂ ምንም አይነት መሻሻል አላሳዬም።የኑሮ ውድነቱ፣ የሰላም ማጣቱና በህይወት የመኖሩ ዋስትና መደብዘዙ፣ድህነቱ፣በጎሳ ማንነቱ መፈናቀሉና መገደሉ በተለይም በአማራው ማህበረሰብ ላይ የሚደርሰው ሰቆቃና ጭፍጨፋ እያደር ጨመረ እንጂ አልቀነሰም።

ግፍና በደል የወለደው የአማራ ፋኖን ለማጥፋት የተጀመረው ማሳደድና በአገር መከላከያ ደረጃ የተከፈተበት ዘመቻ ያሰበውን ውጤት ባያመጣም ብዙዎቹን ከቀያቸው እንዲኮበልሉና ጫካ እንዲገቡ ሲያደርግ ብዙዎቹንም በከበባ ህብረተሰቡን አስጨንቆ ነጥሎ ለማሰር በተደረገው ጥረት ሁሉንም ባይሆን በሽህ የሚቆጠሩትን የሚሊሺያና የልዩ ሃይል አባላት እንዲሁም ፋኖዎችን ለማሰር ችሏል። ጋዜጠኞችን፣የማህበረሰብ አንቂዎችን፣የሕግ ባለሙያዎችን፣የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ሳይቀሩ ሕገወጥ በሆነ እርምጃ ታፍሰው በጨለማ ቤት የታጎሩትን ቤት ይቁጠራቸው ከማለት ባለፈ ቁጥራቸው ስንት እንደሆነ፣የትና መቼ እንደታሰሩ፣በሕይወት ይኑሩ አይኑሩ የሚታወቅበት መንገዱ እዬጠበበ መጥቷል። ለይስሙላ ፍርድ ቤት ቀርበው በገንዘብ ዋስትና የተለቀቁትም ቢሆኑ ገንዘብ ከከፈሉ በኋላ እስርቤት በር ላይ ጠብቆ ለሌላ እስራት የሚዳረጉ ሆነዋል።ክልል አስሮ የፈታውን ፌዴራል ሌላ ክስ መስርቻለሁ ብሎ የሚያስርበት የፍትህ ትርጉም ያጣበት አገር ሆናለች። አንዳንዶቹም ይህንን ፍትሕን በዱላ የሚጠለዝባት አገር ሲሉ ሰይሙታል።ፍርድ ቤት የገንዘብ ዋስትና ማስቀመጡም አዲስ የገንዘብ ማስገቢያ ምንጭ ተደርጎ የተወሰደ እንጂ በሕግ አንጻር አስፈላጊነቱ እስከዚህም ነው የሚሉ አልጠፉም።የሕግ ባለሙያዎች እንደሚሉት ጉዳዩ እስኪጣራ ድረስ ተጠርጣሪ ሲፈለግ ለመቅረብ የሰው ወይም የገንዘብ ዋስትና ማቅረቡ የተለመደ ነው።ወንጀሉ ሳይረጋገጥበት ግን ማሰርና ማጉላላት ብሎም ለፍርድ መቅረብ አይኖርበትም ይላሉ።ፍትህ በሰፈነባቸው አገሮች ከመጠርጠር መዳን ባይቻልም ያልተረጋገጠበት ተጠርጣሪ አይታሰርም፤ዳኛም አይፈረድበትም።እንኳንስ ተጠርጣሪ

የተረጋገጠበት ወንጀለኛም ቢሆን በታሰረበት ወቅት ለደረሰበት ጉዳት፣የስነልቦና ስብራትና አልፎ ተርፎም በእስር ቤት በድብደባ ለሚደርስበት የአካል መቁሰልና መጎዳት ካሳ ማግኘት ሕጋዊ መብት ነው።በሃሰት ወንጀል የከሰሰና ፍርድ የሰጠም ዳኛና የፍትህ ተቋም ለደረሰው ሁሉ ተጠያቂ ይሆናል። በአገራችን ግን እነዚህ ሁሉ የሰማይ ያህል የራቁ የምኞት ዓለም ጸጋ ናቸው።ባልፈጸመው ወንጀል ወይም በቂም በቀል ተገዶ በሰላም እጁን የሰጠ ዜጋ እንደ ምርኮኛ ተቆጥሮ የሚፎከርበት አገር ቢኖር ኢትዮጵያ ነች።መሣሪያ ያላነገበ፣ግን የብሶት ድምጹን ለማሰማትና ፍትሕ ለመጠዬቅ አደባባይ የወጣ ዜጋ በጥይት የሚደበደብባት አገር ብትኖር የኛይቱ ኢትዮጵያ ነች።ዜጋ በጎሳ ማንነቱና በእምነቱ የሚጨፈጨፍባት የሚፈናቀልባት፣ለብዕር መትረዬስ የሚደቀንባት አገር ብትኖር የኛይቱ ኢትዮጵያ ነች።በሕዝብ ስም የሚሰበሰብ የእርዳታና የብድር ገንዘብ ለአምባገነኖች የግል ሥልጣንና የተመቻቸ ብሎም የቅብጠት ኑሮ የሚባክንባት አገር ብትኖር ኢትዮጵያ ነች።በሥልጣን ላይ ያሉ መሪዎች ምን እንደሠሩ፣የት እንደሄዱ ፣ከማንጋር ምን እንደተዋዋሉ የማይጠዬቁባት፣ አገር የግል ንብረት የሆነባት ብትኖር ኢትዮጵያ ናት። በነዚህና በመሳሰሉት መለኪያዎች ስንመዝን አገራችን ኢትዮጵያ የሕዝብ አገር ሳትሆን የሕዝብ እሥር ቤት ነች ማለቱ ከእውነት መራቅ አይሆንም።

ላለፉት ሦስት ሳምንታት በሕዝቡ ልቦና ላይ ጥርጣሬና ስጋት ያሳደረበት ጉዳይ ቢኖር አንዱ የመሪው የአብይ አህመድ መሰወር ነበር።አብይ አህመድ የአገሪቱ ጠ/ሚኒስቴር ነው ቢባልም የኢትዮጵያ ጠ/ሚኒስቴር ሳይሆን የኦሕዴድ/ኦነግ መሪ ነው ማለቱ የሚሠራቸው ሥራዎች ያረጋግጣሉ።ለሱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኢምንት ነው፤ያሻውን ያደርጋል።ሲፈልገው ጣጥሎት ይደበቃል፣ሲያሻው ብቅ ብሎ ያሻውን ይቀደድበታል።ታዲያ ይህንን ከንቱ ምግባሩን የሚያሞግሱ አድር ባዮችና አጨብጫቢዎች እንደ ልዩ ስጦታና ችሎታ እዬቆጠሩ ሕዝቡን ሲያደናግሩት ከርመዋል። አንድ ጊዜ በሸኔ ላይ የሚዘምተውን ጦር እዬመራ ወለጋ ሄደ፣በጥይት ተመቶ ቆሰለ፣ሌላ ጊዜ ታሞ ቱርክ ለህክምና ተጓዘ፣በሌላ ጊዜ ዱባይ ቀጥሎም ቤልጅዬም በህክምና ላይ ይገኛል እያሉ ሁሉንም ሆነ ብለው የለፈለፉበት ምላሳቸው ሳይደርቅ፣ አብይ አህመድ ተኳኩሎ ብቅ ማለቱን በፎቶ በታጀበ ዜና ሰምተናል።እውነት ይሁን አይሁን ለማመን የሚያስቸግረው በተሰወረበት ጊዜ ብዙ ሊያልፉቸው የማይፈልጋቸው ሁኔታዎች ተከስተው ባለመታዬቱ በተጨማሪም የቆዬ የስብሰባ ምስል ነው፣በህይወት የለም የሚለውን ትችት ይዘን የሽመልስ አብዲሳና የአባ ዱላ ገመዳን ለአንድ ቀን ደርሶ መልስ ዱባይ መጓዛቸውን ስንሰማ ጥርጣሬያችንን ከፍ ያደርገዋል።እንደ ሰው ክፉ ነገር ባንመኝም ሕዝቡ እውነቱን የማወቅ መብቱ ይከበርለት እንላለን።ይህ በራሱ መንግሥትና ሕዝብ የተራራቁ መሆናቸውን ያሳያል።

በዚሁ በቴሌቪዥን በተላለፈው ስብሰባ ላይ አብይ አህመድ የብልጽግና ተከታዮቹን ሰብስቦ የሰጠው ማብራሪያ ስለከረመበት ሁኔታ ሳይሆን ስለኤኮኖሚ እዚያና እዚህ ዬተምታታ ገለጻ ሲሆን እንደተለመደው በአግራሞት እራሳቸውን እዬነቀነቁ በልባቸው አቤት የእኛ ጌታ ፣ከፈጣሪ በታች ያለ አዋቂ መሪያችን በማለት ሲያደንቁ ከማዬት በቀር አንድም የካቢኔ አባል ተብዬ ዬት ከረምክ?ለምንስ እውነቱ ለሕዝቡ አይገለጽም ያለ ደፋር አገር ወዳድና ለተቀመጠበት ወንበር ያደረ ሰው አልታዬም።

የንቀቱ ንቀት ስለማይክሮ ኤኮኖሚክስ ሲተነትን እንደምሳሌ ያቀረበው ወተትን ነው። ከላም የሚታለበው ወተት የሚጠጣና የሚሸጥ መሆኑን እርጎ ፣አሬራ፣አይብ፣ ቅቤና ፣አጓት እያለ ሲተነትን፣ ከፊቱ የተደረደሩት አጫፋሪዎቹ ፍጹም ወተት አይቶ እንደማያውቅ ሆነው ላም አለኝ በሰማይ በሚል ስሜት ውስጥ ተውጠው ምራቃቸውን ከመዋጥ ባለፈ ለመሆኑ ላሟና መኖው ከዬት ይመጣል ብሎ የጠዬቀ የለም።የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ ወተት ጥቅምና ና ከወተት ለሚገኙ ተከታታይ ምርቶች እንግዳና ባዳ አይደለም፤ለቀባሪው አረዱት ይሏል ይህ ነው።በድርቅ እንኳንስ እንስሳት የሰው ልጅ እንደቅጠል በሚረግፉባት አገር ውስጥ ተቀምጦ ዘይት በጠፋበት አገር ስለ ቅቤ ማውራት በሰው ቁስል እንጨት

ስደድበት ይሆናል።ይህንን የሰማ ከብቶቹ በድርቅ የረገፉበት የነገሌ ቦረናና የአፋር አርብቶ አደር ምን ይል ይሆን?የኢትዮጵያ ሕዝብ ምግብ አጣ እንጂ ስለአመጋገቡ ዝግጅት ያውቅበታል። ይህንን አይነቱን መዘላበድ ሲመለከቱ ነው ብዙ ታዛቢዎች አብይ የጤና መቃወስ አለበት የሚሉት።እውነትም ከጤነኛ አይምሮ የሚፈልቅ አስተያዬት አይደለም።የማክሮ ኤኮኖሚንና የሚክሮ ኤኮኖሚንም ልዩነት ያጤነው አይመስልም፤ተምታቶበታል። ይህንን በተመለከተ የኤኮኖሚክስ ባለሙያዎች ይጨነቁበት።

በዚህም አላቆመም ስለጫካ ልማትም ያለውን ብሏል።የዘነጋው ቢኖር ከሁሉም ልማት በፊት የሰው ልጅ ወይም አገርና ሕዝብ መኖር እንዳለባቸው ነው።ሕዝብ እዬተፈናቀለ፤እዬታረደና እይተጨፈጨፈ፣ የዜግነት ስሜት ሳይኖረውና መብቱ ሳይከበር ጫካ ቢያለብሱት ለዱር አራዊት መፈንጫ ይሆናል እንጂ አገር አይሆንም።አገርን አገር የሚያሰኘው የሰው ልጅ በሰላም መኖር ሲችልና የመኖር ጥያቄው ሲመለስለት ነው። ጫካውም መዝናኛ የሚሆነው ሌላውን ጥያቄ መልሶ ለመዝናናት ና በተፈጥሮ ጸጋ ለመደሰት ከሚያስብበት ደረጃ ላይ ሲደርስ ነው።ውሃ የጠማው ሕዝብ ስለዋና ቦታ ፤የተራበም እንዲሁ ስለተትረፈረፈ የብፌ ገበታ አያስብም።

ሌላው የሚያስቀው ነገር መቸም መሳቅ የማድነቅ ብቻ ሳይሆን የትዝብትም ሳቅ አለና! ስለሌብነት የሰጠው አስተያዬት ነው። ሌባ ማለት ከሰው ኪስ ውስጥ ገብቶ የመነተፈ፣ወይም ቤትና መጋዘን ሰብሮ የዘረፈ ብቻ ሳይሆን በአገር ደረጃም ሥልጣን ይዞ የአገርና የሕዝብ ንብረትና ሃብት ሙጥጥ አድርጎ መዝረፍና ማዘረፍ ከሌብነት ሁሉ የከፋ ሌብነት ነው።በዚህ ተግባር ላይ የዋለ የሰፈር ሌባ ሳይሆን ብሔራዊ ሌባ ነው።በዚህ የሌብነት ተግባር ውስጥ አብይ አህመድና የሚመራው የጎሰኞች መንግሥት ተብዬው ቡድን ዋናውን ቦታ ይይዛል።ከሚያገኙት ደመወዝ ጋር በማይመጣጠን የኑሮ ደረጃ፣ከአገር አገር ከነቤተሰብ የሚዞሩበትና የሚዝናኑበት ከፍተኛ ወጭ፣በቢሮና በእለታዊ ወጭ የሚያባክኑት መጠነ ብዙ ብር፣በአገር ውስጥ ብቻም ሳይሆን በያገራቱ በተለይም በአረብ አገራት፣በአውሮፓ፣በአሜሪካና በእስያ ከተሞች የሚገዟቸው ዘመናዊ መኖሪያ ቤቶች፣ ሆቴሎችና በዬትላልቅ የንግድ መስኮች የሚያውሉት የገንዘብ ሽርክና ተፋሰስ ከዬት የመጣ ነው?ሌቦች እያለ የሌባ ጣቱን ወደ ተራው የቢሮ ሰራተኛ ሲጠቁም የቢሮ ሠራተኛውን ማን አስተማረው ብሎ መጠዬቁን የረሳው ይመስላል።አንድ ጣት ወደሌላው ሲሆን ሦስቱ ጣት ግን ወደራስ መሆኑን ዘንግቶታል።ዳኞችንም በሌብነት ወርፏል።ሌቦቹን ከሚሰርቁበት ወንበር ላይ ማን አስቀመጣቸው?ተከተል አለቃህን ብለው ቢሰርቁ የመጀመሪያው ተጠያቂ የሆነው ሳይጠዬቅ እንዴትና በዬትኛው ሕግ ሊጠዬቁ ይችሉ ይሆን?አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ በሆነበት አገር ፍትሕ በማንና መቼ ተከብሮስ ያውቃል? ስርዓቱ የቀፈቀፋቸው ሌቦች የሚወገዱት ሥርዓቱ ሲወገድ ብቻ ነው።የአብይ አዝማሚያ ግን በዚህም ውንጀላ ለማሶገድ ያሰበው እንዳለ ያመለክታል ።

ሕዝቡ በተለይም ትውልዱ ለማኝና ገዳይ ሆኗል ሲልም ተደምጧል፣ልመናውን ማን በፊታውራሪነት መራ?እራሱ አብይ አህመድ በኢትዮጵያ ስም ያገኘውን ገንዘብ ለምኜ ያመጣሁት ነው፤ ማንም ሊጠይቀኝ አይገባም ብሎ አልነበረምን?ስለመገዳደሉስ የጎሳ ፖለቲካና አገር አፍራሽ፣ ሕዝብ አጫራሽ የሆነ መመሪያ ሰንድ ተሸክሞ፣ የክልል ልዩ ሃይልና የቡድን ታጣቂ አዘጋጅቶ አገር የሚያምሰው አብይና የሚመራው ቡድን አይደለምን?ሕዝብን ለማጫረስ የአኖሌን ሃውልት ማን በሃሳብና በተግባር ግንባር ቀደሙን ሚና ተጫወተ?የሰው ልጅ ህይወት ዋጋ ካጣበት የደርግ ዘመን ቅጥያ የሆነው እራሱ የተካተተበት የህወሃት ኢሕአዴግና የራሱ አሕዴድ ብልጽግና መንግሥት ዘመን አይደለምን?ታዲያ ትውልዱ ገዳይ ቢሆን ምን ይፈረድበታል?ማንን አይቶ ሰላማዊ ይሁን?በልመናና በስርቆት ሃብት ሲሰበሰብ እያዬ ፤የሥራ ዕድል ሳይኖረው ቢሰርቅና ቢወሰልት ተጠያቂው ማነው?ስርቆትን ከማን ተማረ? ነገሩ ትልቁ ሌባ ትንሹን ሌባ አይወደውም ነው።

በመንግሥቱና በመሪው ዙሪያ ይህንን ካልን ወደሕዝቡ ስንመለስ የሚከተለውን ለማለት እንገደዳለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሌሎቹ አገራት ሕዝቦች በውጭ ወራሪዎች ሳይገዛ ነጻነቱን አስጠብቆ በመኖር የመጀመሪያውን ቦታ ዪያዘ ሕዝብ ነው ቢባልም ባሳለፈው ታሪኩ ያላስተናገደው ጨካኝ መሪና ሥርዓት፣ያልተቀበለው ፈተናና መከራ የለም።በራሱ አገር በቀል መሪዎቹ የደረሰበትና እዬደረሰበት ያለውን መከራ በፍርሃት ቆፈን ታጅሎ በዝምታና በትእግስት በመሸከም የደነደነ ጫንቃ ባለቤት በመሆንም የአንደኛነትን ቦታ ሳይዝ አይቀርም።በሳለፋቸው የስቃይ ዘመናቱ ከውስጡ ነጥረው የወጡ ጥቂት ግፍና መከራ ያስመረራቸው መኖራቸው የሚካድ አይደለም።ሆኖም ግን እነዚህ ደፋር ዜጎች ለተነሱበት ዓላማ ሳይበቁ ተቀጭተው እንዲቀሩ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል ዋናው ከመከራ እንገላግለዋለን ያሉት ህብረተሰብ ያደረገው ዝምታ፣ክህደት፣ ፍርሃትና አሳልፎ የመስጠት እርምጃ ነው።ስለሆነም ከበዳዩ መንግሥት ባላነሰ ደረጃ የሚወቀሰውና ለወንጀሉ ተባባሪ የሆነው ሕዝቡ ነው ለማለት እንደፍራለን። ዝም ማለት በራሱ ተባባሪነት ነው።ወገን ሲጠቃ፣አገር ሰላም ሲያጣና ለመበታተን ሲቃረብ ዝም ማለት የወንጀለኞቹ ተባባሪ መሆን ነው። ዝምታ ከአስከሬን እንጂ ህይወት ካለው ፍጡር አይጠበቅም።እንኳንስ የሰው ልጅ ውሃም ቢሆን ሳይንቀሳቀስ ተከትሮ ከቀረ ይገማል ፣ ይገለማል።የሰው ልጅ ደግሞ ለኑሮው፣ለመብቱና ለነጻነቱ፣ለሰብአዊ ክብሩና ለአገሩ ብሎም ለተተኪው ትውልድ ካላሰበና ካልታገለ በቁሙ ሞቷል ማለት ነው።

ይህ የትናንትና ታሪክ ሳይሆን ዛሬም የሚፈጸም የሕዝብ ድክመት ነው።ዛሬም እንደ ትናንቱ ለመብቱ የሚታገሉለት እዬተሰዉ ነው፣በአረመኔዎች እዬታደኑ ለሞትና ለእስራት የተዳረጉ ብዙዎች ናቸው። ከጭፍጨፋ አምልጦ የሚፈናቀለው ጥቃቱን በመከላከልና በአጥቂዎች ላይ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ አስጨፍጫፊውን መንግሥት እዬለመነና እዬተለማመጠ የሚድን ይመስለዋል።በጎሳ ማንነቱ ሲጨፈጨፍ በጎሳ ማንነት የተቋቋመውን ጨፍጫፊና አስጨፍጫፊ መንግሥት ነኝ ባይ ቡድን ይማጸናል፤ጠላትና ወዳጁን አለዩም።

በዚህ የልብ ልብ የተሰማቸው አገር አጥፉ ቡድኖች በሥልጣን ምክንያት የሚያደርጉትን ግብ ግብ አቁመው አገር በማፈራረሱ የጋራ ዓላማቸው ላይ በመስማማት በዬፊናቸው እዬመከሩና እዬተመካከሩ ነው።ወያኔና ብልጽግና የተባሉት ከአንድ ምንጭ የተቀዱ መርዞች በመካከላቸው ያለውን የሥልጣን ሽኩቻ በመግባባትና ለሁለቱም በሚያረካ መልኩ አብሮ ለመሥራት በውጭ ሃይሎች ጣልቃ ገብነት ስምምነት ላይለመድረስ ተቃርበዋል።የአገር ጉዳይ በአገር ሽማግሌዎች መፈታት ሲቻል የውጭ ሃይሎች እንዲገቡበት ማድረጉ አገራችንን ለቀጣይ ባርነት ይዳርጋል።በዚህ የጋራ ስምምነት የሚጎዳው ኢትዮጵያዊነትና ስለኢትዮጵያ ጠንካራ አቋም ያለው ማህበረሰብ ነው።

አብይ አህመድ የአውሮፓና የአሜሪካ ዲፕሎማቶችን ተቀብሎ አለማነጋገሩ በተሰወረበት ምክንያት ነው ቢባልም በእኛ ግምት ለተደረሰው ስምምነት እራሱን ነጻ ለማድረግና በቦታው የነበሩትን ተጠያቂ ለማድረግ ይመስለናል።ይህም ካለፉት እኔ አላውቅም ከሚለው አባባሎቹ በመነሳት ነው።የማይካደው ቢኖር በቦታው የነበሩትም ከሱ እውቅናና መመሪያ ውጭ እንደማይንቀሳቀሱ ነው። የስምምነቱን ውጤት የምናዬው ይሆናል።ገና ከጅምሩ አንዱ ሌላውን እዬከሰሰ መጥቷል።

የመደራደሪያ ዋና አጀንዳ የሆነው የራያ አዘቦ፣የወልቃይትና ጠገዴ ሰፊና ለም መሬት ከታሪካዊ ባለቤቱ ከቤጌምድርና ከወሎ ሕዝብ እጅ ነጥቆ ለወያኔ ማስረከቡ ወይም አለማስረከቡ የድርድሩ መቋጫ ወይም መፍረሻ ይሆናል።የአብይ መንግሥት እሰጣለሁ ቢል የአማራ በተለይም የቤጌምድር ሕዝብ አሳልፎ ይሰጣል ማለት አይደለም።የወሳኙ ጦርነት መንስኤ ይሆናል። በተለይም የወልቃይትና ጠገዴ መሬት ከለም አፈሩ በላይ ካለው ስትራቴጂካዊ አቀማመጡ የተነሳ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው አካባቢ

ነው።ወያኔ ወልቃይትን የሙጥኝ የሚለው ለመገንጠል ካለው እኩይ ዓላማ በመነሳት ከውጭ አገራት በተለይም ከሱዳን ጋር የመገናኛ በር እንዲኖረው ከመሻት እንጂ ለትግራይ ደሃ ሕዝብ ጥቅም አስቦ አይደለም።ባለፉትም 27 ዓመታት በመዳፉ ውስጥ በተቆጣጠረበት የሥልጣን ዘመኑ ለጥቂት የህወሃት ባለሥልጣኖች እንጂ ለተራው የትግራይ ሕዝብ ከወቅታዊ የሥራ ዕድል ባለፈ(seasonal worker) የሰጠው ጥቅም የለም።

አረቦችና ምዕራባውያን በወያኔ ጀርባ በመቆም ዓይናቸውን ከጣሉበት የኢትዮጵያ ክፍል አንዱና ቀዳሚው ቦታ ወልቃይት ነው።አማራው ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያን የሚወድ ሁሉ ይህንን ከባቢ ለማዳን በትግሉ መሳተፍ ይኖርበታል።ወልቃይት የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ቀንድ ከባቢ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ምሰሶ ነው።ወልቃይትና ራያ እንዲሁም ሌላው የኢትዮጵያ መሬት የሁሉም ዜጋ ንብረት እንጂ አንድ ነጠላ ጎሳ የሚያዝበት መሆን የለበትም።ሁሉም ዜጋ በፈለገበት ቦታ ሄዶ የመኖርና የመሥራት ፣ሃብትም የማፍራት መብቱ ሊከበርለት ይገባል።ይህ የማይናወጥ አቋማችን ነው።ጥንትም ቢሆን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወልቃይት ውስጥ እዬኖረ የሚችለውን ሥራ ሠርቶ፣ከኑዋሪው ጋር ተጋብቶና ተዋልዶ ኑሮውን ይገፋ ነበር።ቦታዎች ለአስተዳደር በሚመቹ መልክ በክፍለሃገር ይዋቀሩ ስንል ለሕዝቡ ኑሮና ሰላም አመችነታቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት እንጂ አንዱን ባለቤት ሌላውን ባይተዋር የሚያደርግ ስርዓት ይስፈን ማለታችን አይደለም።ለሶማሌው አክሱም እንደ ትግሬው ተወላጅ እኩል ንብረቱ ነው።ለትግራዩም ጅግጅጋ እንዲሁ።ጋምቤላ ለአፋር ሕዝብ እኩል ንብረቱ ነው፤ አፋርም ለጋምቤላው እንዲሁ፤ሌላ ሌላውም ። በዚህ ህሳቤ አገራችንን መልሰን ለማዋቀር አሁን ያለውን የጎሰኞች ስርዓትና የሚመሩበትን የጥፋት ሰነድ(ሕገ -ጥፋት)ማስገድ የግድ ይላል።የኢትዮጵያን መሬት የጎሳ ማንነት መስጠት ዜጋ በኢትዮጵያዊነቱ በፈለገበት ቦታ ሄዶ እንዳይኖር መከልከል ማለት ነው።የሚታዬውን የጎሳ ጭፍጨፋና መፈናቀል መፍቀድና መቀበል፣አንዱን ባለቤት ሌላውን መጤና ባዳ ማድረግ ማለት ነው።

ከወልቃይት ወጣ ስንል ደግሞ በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚካሄደው የኦሮሙማው የተረኝነትና የፈላጭ ቆራጭነት እርምጃም በሰፊው ቀጥሏል።የአነግን ባንዲራ ከመስቀልና የአነግን መዝሙር ከማዘመር ድፍረት አልፎ ከአማራው ክልል ብቻ ሳይሆን የአማራነት መታወቂያ የያዘ የከተማዋ ነዋሪ ወጥቶ ሊገባ አልቻለም።ከወሎና ከጎጃም ከሸዋ የሚመጡ የአማራ ክልል መታወቂያ የያዙ ዜጎች ከተማ እንዳይገቡና ወደመጡበት እንዲመለሱ ከከተማዋ የቅርብ እርቀት ላይ ታግደዋል።ለሕክምና የሚሄዱ ለብዙ ችግር ተጋልጠዋል።ይህ አዲስ አበባን ነጥቆ የመሰልቀጡ ዓላማ አንዱ መንገድ ሲሆን ነገ በከተማዋ ውስጥ የሚኖረው ኦሮሞ ያልሆነውና ያልገበረው ኢትዮጵያዊ በተለይም የአማራ ተወላጅ ንብረቱን ተነጥቆ በነቂስ እዬተለቀመ ወደመጣበት ወይም በተዘጋጀለት ክልል በተባለ እስርቤት እንዲጠቀጠቅ እነ ዲማ ነገዎ ባቀዱት አነጋዊ እቅድ መሰረት ላለመፈጸሙ ዋስትና የለም።

በዚህ ሥልጣኑንም መሬቱንም በመሰልቀጥ ሽሚያ የተሰለፉት የተለያዩ የኦሮሞ ድርጅት ነን ባዮች እርስ በርሳቸው ሲነታረኩ ይታያል።በጋራ ዓላማቸው በሆነው ኢትዮጵያን አፍርሶ ኦሮሚያ የተባለ አገር መመሥረት በሚለው ቢስማሙም በጥቅምና በሥልጣን ድርሻ ላይ ልዩነት ፈጥረዋል።ይህ ማለት ግን ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን የተሻለ ሰላምና ኑሮ ያመጣሉ ማለት አይደለም።አንዳንዶቹም እንደ ጁዋር ሞሃመድ ያሉ በብዙ ህይወት መጥፋት ተጠያቂ የሆኑ ወንጀለኞች በአንድ ጀንበር ኢትዮጵያን የሚጠቅምና የሚያስከብር አቋም በያዘ መልኩ መዘላበድ ጀምረዋል። ይህ ሕዝቡን ለማማለል የሚደረግ ሙከራ ሕዝቡን ከመናቅ የመነጨ እንጂ ከቅንነት አይደለም።ከቅንነት የመነጨ ቢሆንማ ኖሮ በወለጋና በተለያዩ ቦታዎች ለፈሰሰው የንጹሃን ደም ተጠያቂዎቹን ይፋ በማድረግ ለፍርድ ይቅረቡ ባሉ ነበር፤እራሳቸውም ለፈጸሙት ጥፋት ይቅርታ በጠዬቁ ነበር።በሃሰት ትርክት ያቆሙትን የአኖሌን

ሃውልት ባፈረሱ ነበር።የነጻነት ምልክት የሆነውን፣ጎሳና ሃይማኖት የማይለዩውን አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርገው ባውለበለቡት ነበር።ተምረው የሚናገሩበትንና ከሁሉም ኢትዮጵያዊ ጋር የሚግባቡበትን የአማርኛ ቋንቋ ለሌላው አዲሱ ትውልድ የኦሮሞ ወጣት ዕድሉን ባልነፈጉትና በባዕዳን ፊደል እንዲጠቀም ለባርነት ባልዳረጉት ነበር።

የዘረዘርናቸውን ሁለገብ ችግሮች በከፊሉ ለማጠቃለልና ወደ መፍትሔው ስናመራ የተጋረጠብንን የመኖርና ያለመኖር ፈተናና አደጋ መዝለቅ የሚቻለው በጠንካራ አንድነት ራዕይ ባለው ትግል መሳተፍ ስንችል መሆኑን ደግመን ደጋግመን እናሳስባለን።ከዚህ ውጭ ሌላ አማራጭ የለም።

በመጽሃፍ ውስጥ ባገኘናቸው "የፍርሃት ግምብ ይፍረስ!"እና "ምን ነካው ሃበሻ" በሚሉ የግጥም መልእክቶች የዛሬውን አገር እንዴት ሰነበተች ቅንብራችንን እንደመድማለን።

የፍርሃት ግምብ ይፍረስ!

ሲያስጠቃን የኖረው እስከ ዛሬ ድረስ፣

ከእንግዲህ ይበቃል የፍርሃት ግምብ ይፍረስ።

ኑሮም አንዴዬ ነው፣ሞትም አንደዬ ነው፣አማራጭ የለውም፣

በፍርሃት በስጋት አናሰግደውም።

የተንጠለጠለ በሕዝብ ትከሻ ፣

የፍርሃት መንደር የፍርሃት ዋሻ፣

ይፈርሳል ይናዳል አለው መጨረሻ።

ሲበሉም ይሞታል፣

ሲጠጡም ይሞታል፣

ሲሸሹም ይሞታል፣

ታመውም ይሞታል፣

ፈርተውም ይሞታል፣

ደፍረውም ይሞታል፣

ለነጻነት መሞት፣

ለእኩልነት መሞት፣

ለአንድነት መሞት፣

ላገር ክብር መሞት

ይሻላል ተንቆ ከመኖር በህይወት ።

የተመለከተ ያዬ ምን ይለናል፣

ፍርሃት የገደለው አስከሬን ሆነናል።

አገሬ አዲስ

ጥቅምት 2004 ዓም

## ምን ነካው አበሻ?

አገር በመውደዱ በኢትዮጵያዊነቱ፣

ካለማው መሬቱ፣

ካፈራው ንብረቱ፣

ከቀለሰው ጎጆ፣ ከኖረበት ቤቱ

ከተወለደበት ካደገበት መሬት፣

ባዳ መጤ ብለው ነቅለው ሲያባርሩት።

ዓለም በማያውቀው በጭካኔ መንገድ ፣

ጽንስ ሲሸለቀቅ ህጻን ልጅ ሲታረድ፣

አንገት ከመድፋቱ፣

እንባ ከመንዛቱ፣

ምናለ ባንድነት ቢታገል ለመብቱ?

መስጊድ እንደገባ እንዳበደ ውሻ፣

እየቀጠቀጡ ሲያሳጡት መድረሻ፣

ግፍ አይመረውም ወይ?በቃኝ አይልም ወይ?

ምን በጥብጠው ጋቱት?፣ምን ነካው አበሻ?

ህያው ፍጡር ሆኖ የማይንቀሳቀስ፣

ቢፈለጥ ቢቆረጥ ቢቀቀል ቢጠበስ፣

ወይ እረመጥ አይሆን፣ ወይ አይነድ ወይ አይጨስ፣

ብሶት በማሰማት በመጮህ በማልቀስ

ማን እስኪመጣለት እስከመቼ ድረስ?

ወይስ ይጠብቃል ዳግመኛ ምጽአት ፤ ዳግመኛ ክርስቶስ?

ትናንትና ደርጎች

እነዚያ ሰው በሎች፣

ከደጁ ዘርግተው የልጁን እሬሳ፣

እንዲመለከተው ማለዳ ሲነሳ፣

የገደሉበትን የጥይቱን ዋጋ አንቀው ሲያስከፍሉት፣

በልጁ አስከሬን ላይ ጨፍር፣ ፎክር ሲሉት፣

ፍትህ ሳይወርድለት ሃዘኑ ሳይወጣ፣

ደግሞ ይባስ ብሎ ኢሕአዴግ መጣ፣

በጎሳ ሸንሽኖ ካገር የሚያባርር፣አገር የሚያሳጣ።

ሁሉንም እሺ ሲል እንዳልተበደለ፣

እየተዘረፈ፣እየተገደለ፣

አምባገነኖችን እዬተቀበለ፣

የባሰ አያምጣብኝ ተመስገን እያለ፣

ምን ነካው አበሻ እንዲህ ነሆለለ?

የመከራ ጽዋ ዞትር እየጠጣ፣

በቃኝ አሻፈረኝ ብሎ ማይቆጣ፣

ምን ነካው አበሻን አረ ምን ጉድ መጣ?

መከራና ችግር የማያስተምረው፣

መበደል መጠቃት መስቃ የማይመረው፣

በምን እጁ፣ይሆን በየትኛው እለት አምላክ የፈጠረው?

በየትኛው ቋንቋ፣በየትኛው ትርጉም፣

ቢነግሩት ይረዳል የነጻነትን ጣእም።

ዶሮ እንኳን ጫጩታን ጭልፊት እንዳይበላው፣

ትከላከላለች በክንፏ ከልላው።

ትዕግስት ነው አይሉት ትዕግስት ድካ አለው፣

ምን ይሆን ምክንያቱ አንደበቱን ዘግቶ ዓይኑን የከለለው?

ሲባል የነበረ ጀግናና ታታሪ፣

ምን ለከፈውና እንዲህ ሆነ ፈሪ?

ወይስ ጥቅም ገዛው ሆነ ሆድ አዳሪ።

አህያ እንኳን ባቅሙ አለንጋና ስቃይ ጭነት ሲበዛበት፣

አሻፈረኝ ይላል፣

ይነከሳል ፣ያምጣል፣

ጭነቱን ለመጣል፣

ይዘላል ይሮጣል ።

አበሻ ደግ ነው ያሉትን ያደርጋል፣

መብቱን ያስደፍራል መሪ ያባልጋል።

ደፍሮ እምቢ ካላለ፣

በአንድነት ካልቆመ፣ በዚህ ከቀጠለ፣

የባሰ ይሆናል ካደረ ከዋለ።

ህሊናውን ከዶ ለሆዱ ካደረ ፣

ዘላለም ይኖራል እንደተደፈረ።

ለጊዜያዊ ጥቅም እራሱን ከሸጠ፣

ተዋርዶ ይኖራል እዬተረገጠ።

እግር ወዲያ ሄዶ እግር መጣ ወዲህ፣

እጅን የሚያወጣው እጅ ነው ከእንግዲህ።

መጋቢት 2005 ዓም